BBC LEARNING ENGLISH

# Essential English Conversation

## How often do you play football?

## እግር ኳስ ምን ያህል ትጫወታለህ/ቻለሽ?

*This is not a word-for-word transcript*

**ምህረተስላሴ**
ጤና ይስጥልን። ማንኛውም የእንግሊዝኛ ተማሪ ማወቅ የሚገባውን የቋንቋ መሰረታዊያን ወደሚያቀርበው Essential English Conversation እንኳን በደህና መጡ። ምህረተስላሴ እባላለሁ። በዚህ ክፍል ሰዎች በህይወታቸው ውስጥ አንዳንድ ነገሮችን በምን ያህል ድግምግሞሽ እንደሚያደርጉ መናገርን ይማራሉ።
ሁለት ሰዎች ነግሮችን ምን ያህል ደጋግመው እንደሚያደርጉ ሲነጋገሩ እናዳምጥ።

***Lisa***
*How often do you play football?*

***David***
*I play football once a week. How about you?*

***Lisa***
*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
ይህ አስቸጋሪ ቢሆንብዎት ብዙም ጭንቀት አይግባዎት፤ ውይይቱን ከፋፍለን እንዲለማመዱት እናግዝዎታለን።
በመጀመሪያ ሊሳ ዴቪድን 'How often do you…?' አለችና 'play football' ን በማስከተል እግር ኳስን ምን ያህል ደጋግሞ እንደሚጫወት ጠየቀችው። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*How often do you play football?*

**ምህረተስላሴ**
ከዚያ ዴቪድ "በሳምንት አንዴ እግር ኳስ እጫወታለሁ" 'I play football once a week' ብሎ መለሰላት። በሳምንት ሁለት ጊዜ የሚጫወቱ ከሆነ 'twice' ን መጠቀም ይችላሉ። ሦስት እና ከዚያ በላይ የሚጫወቱ ከሆነ ደግሞ ቁጥሩን እና 'times' የተባለውን ቃል አንድ ላይ በማድረግ መግለፅ ይችላሉ። ለምሳሌ 'five times' አምስት ጊዜ ማለት ነው።
ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*I play football once a week.*

**ምህረተስላሴ**
ከዚያም ዴቪድ 'How about you?' በማለት ተመሳሳይ ጥያቄ መልሶ አቅርቦላታል። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*How about you?*

**ምህረተስላሴ**
ሊሳ በሳምንት ሁለት ጊዜ ገደማ እንደምትሮጥ መለሰችለት። 'About' የሚለውን ቃል የምንጠቀመው የተግባሩን አንጻራዊ መጠን ለመግለፅ ነው። ሳምንት 'week' የሚለውን ቃል ወደ ቀን 'day' ወይም ወደ ወር 'month' አልያም


© British Broadcasting Corporation 2018

ወደ ዓመት ‘year’ መቀየር ይችላሉ። እናም ‘once a day’ ‘once a month’ ወይም ‘once a year.’ ማለት ይችላሉ። ያዳምጡና ደግመው ይበሉ።

*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች ነገሮችን ምን ያህል ጊዜ እንደሚያደርጉ ሲጠያየቁ በማዳመጥ እርስዎ ካሉት ጋር ያመሳክሩ።

*How often do you play tennis?*

*I play tennis twice a month. How about you?*

*About three times a month.*

*How often do you play basketball?*

*I play basketball twice a week. How about you?*

*About twice a year.*

**ምህረተስላሴ**
እሺ፤ አሁን ያንን ደግመን እንሞክረው። የእንግሊዝኛውን አረፍተ ነገር ያዳምጡና ደግመው ይበሉ። እያንዳንዳቸውን ሁለት ሁለት ጊዜ ያዳምጧቸዋል።

*How often do you play football?*
*How often do you play football?*

*I play football once a week.*
*I play football once a week.*

*How about you?*
*How about you?*

*About twice a week.*
*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
ግሩም፤ አሁን እንግሊዝኛውን ምን ያህል እንዳስታወሱ እንይ። አረፍተ ነገሮቹን በአማርኛ ያዳምጡና የእንግሊዝኛ አቻቸውን ይበሉ።

*ምን ያህል ደጋግመህ እግር ኳስ ትጫወታለህ?*
*How often do you play football?*

*እግር ኳስ በሳምንት አንዴ እጫወታለሁ*
*I play football once a week.*

*አንቺስ?*
*How about you?*


© British Broadcasting Corporation 2018

*በሳምንት ሁለት ጊዜ አካባቢ*
*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ግሩም፥ አሁን ሰዎች ነገሮችን ምን ያህል ደጋግመው እንደሚያደርጓቸው መጠየቅ አውቀዋል። ለሊሳ ምላሽ በመስጠት ልምምድ ያድርጉ። 'How about you?' በማለት ተከታይ ጥያቄ ማቅረብ አይዘንጉ።

*How often do you play football?*
*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
አሁን ሙሉውን ንግግር ያዳምጡና መልስዎን ያመሳክሩ።

***Lisa***
*How often do you play football?*

***David***
*I play football once a week. How about you?*

***Lisa***
*About twice a week.*

**ምህረተስላሴ**
በጣም ጥሩ፤ አሁን ሰዎች ነገሮችን ምን ያህል ደጋገምው እንደሚያደርጉ በእንግሊዝኛ መጠየቅ ችለዋል። ኢጋር ይፈልጉና ነገሮችን ምን ያህል ደጋገመው እንደሚያደርጉ በእንግሊዝኛ በመጠየቅ ይለማመዱ። ለተጨማሪ የኢሴንሻል ኢንግሊሽ መሰናዶ በሚቀጥለው ክፍል ይጠብቁን። Bye!


© British Broadcasting Corporation 2018